www.abyssinialaw.com



11ኛ አመት ቁጥር 27
11th Year No

ባህር ዳር ነሐሴ 12 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar 18 th, August 2006

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 1.65 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box |

| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 42/1998 ዓ.ም | Regulation No.42/2006 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ምክር ቤት ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Intellectual Property Protection Council Establishment, Council of Regional Government Regulation. |

## ደንብ ቁጥር 42/1998 ዓ.ም

### በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ምክር ቤትን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## REGULATION NO.42/2006

### A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE REGIONAL INTELLECTUAL PROPERTY PROTECTION COUNCIL IN THE AMHARA NATIONAL STATE

www.abyssinialaw.com



የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ለአንድ ሃገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ፤

WHEREAS, the protection of the intellectual property immensely contributes for a counter's social and economic development thereof;

መንግስት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለዚሁ ዘርፍ ልማትና ህጋዊ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ላይ ከመሆኑ የተነሣ አበረታች ውጤቶች መመዝገብ መጀመራቸው የታወቀ በመሆኑ፤

WHEREAS, it is acknowledged that encouraging results have commenced to be registered due to the government's proper attention being rendered to wards the development and legal protection of the sector as from recent times;

ሁሉንም የአዕምሯዊ ንብረት አካላት የሚያስተዳድር ሃገር አቀፍ የአዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ተቋቁሞ አቅም ለመገንባት ጥረት እየተደረገ ከመሆኑም በላይ ጽ/ቤቱን በቅርብ የሚያማክርና አቅጣጫ የሚሰጥ ብሔራዊ የአዕምሯዊ ንብረት ም/ቤት ተደራጅቶ ሥራ ከመጀመሩ የተነሣ የአዕምሯዊ ንብረት መብት ገሰሳን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎች ተጠናክረው መቀጠል ያለባቸው በመሆኑ፤

WHEREAS, besides the establishment of a Nationwide Intellectual Property office which is bound to administer all the intellectual property bodies and the ongoing effort being exerted towards capacity building, a National Intellectual Property Council that is responsible to closely consult and provide direction to the office has been set up, started functioning and thus, measures to be taken with the view to preventing an infringement of intellectual property rights have to continue with full swing;

ለዚህም ያመች ዘንድ በክልል መንግስታት በኩል ከአዕምሯዊ ንብረት ም/ቤትና ከብሄራዊ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ለፈጠራ ስራ ጥበቃ አጋዥ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን የሚከታተልና አመራር የሚሰጥ ክልል አቀፍ አካል ይቋቋም ዘንድ የኢፌዴሪ የሚኒስትሮች ም/ቤት ግንቦት 13 ቀን 1996 ዓ.ም ባካሄደው 106ኛ ስብሰባው ውሳኔ ያሳለፈ በመሆኑ፤

WHEREAS, in order to facilitate same in the regional states, the council of Ministers of the F.D.R.E has passed a decision in its 106th regular session on May 22/2004, so that there shall be established a Region-wide organ mandated to follow up the activities to support the protection of creative works and thereby provide managerial guidance in cooperation with the intellectual property council and the National office;

www.abyssinialaw.com



የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ም/ቤት ይህንኑ ውሣኔ ተፈፃሚ ለማድረግ በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it, pursuant to the provision of Art. 58, sub. Art. 7 of the revised Regional constitution, hereby issues this regulation as follows with the view to executing the decision hereof.

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የክልል አዕምሯዊ ንብረት ምክር ቤት ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 42/1998 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Regional Intellectual Property Council Establishment, Council of Regional Government Regulation No.42/2006."

## 2. ስለመቋቋምና ተጠሪነት

1. የአማራ ብሔራዊ ክልል አዕምሯዊ ንብረት ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ) አካል በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

## 2. Establishment and Accountability

1. The Intellectual property council of the Amhara National Regional State herein after referred to as "the council" is established as a body by this regulation.
2. The Council shall be accountable to the Head of the Regional Government.

## 3. ዓላማ

ምክር ቤቱ የተቋቋመበት ዓላማ በክልሉ ውስጥ አዕምሯዊ ንብረት በቂና የተሟላ ህጋዊ ጥበቃ የሚያገኝበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ይቻል ዘንድ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በዘርፉ የሚያካሂዷቸውን እንቅስቃሴዎች ማስተባበርና አጠቃላይ አቅጣጫ መስጠት ነው።

## 3. Objective

The objective for the establishment of the council is to coordinate the activities which the pertinent bodies may undertake in the sector and to give a general direction with the view to creating favorable condition in which intellectual property enjoys adequate and complete legal protection and is thereby put into use throughout the regional state.

www.abyssinialaw.com



## 4. ስለምክር ቤቱ አባላት ተዋፅኦና ጥንቅር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ ......................................... ሰብሳቢ
2. የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ ......................................... አባል
3. የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ...... አባል
4. የክልሉ ፍትህ ቢሮ ኃላፊ ........... አባል
5. የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ......................................... አባል
6. የክልሉ ማስታወቂያ ቢሮ ኃላፊ ... አባል
7. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽነር ............ አባል
8. የባህር ዳር ከተማ ከንቲባ ........... አባል
9. የክልሉ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ......................................... አባል
10. በክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ የሚሰየም ሰው ......................................... ፀሐፊ::

## 4. Representation and Composition of Members of the Council

The council shall have the following members;

1. Head, the Regional Capacity Building Bureau …………………….. Chairperson,
2. Head, the Regional Trade & Industry Bureau …………………………….. member
3. Head, the Regional Education Bureau …………………………….. member
4. Head, the Regional Justice Bureau …………………………….. member
5. Head, the Regional Culture & Tourism Bureau …………………….. member
6. Head, the Regional Information Bureau …………………………….. member
7. Commissioner, the Regional Police ……………………............. member
8. Mayor of the Bahir Dar city …..… member
9. President of the Regional Chamber of Commerce ………………………. member
10. A person to be designated by the Regional Capacity Building Bureau ……..… Secretary.

## 5. የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአዕምሯዊ ንብረት መስክ ግንዛቤ የሚዳብርበትንና የፈጠራ ሥራዎች የሚበረታቱበትን ሁኔታ በተመለከተ የክልሉን መንግስት ያማክራል፤

## 5. Powers and Duties of the Council

The council shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Consult the Regional Government with regard to matters by which an awareness is to be raised in the field of intellectual property and thereby creative works are encouraged thereof;

www.abyssinialaw.com



2. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የአዕምሯዊ ንብረት መብት ገሰሳ የሚገታበትን መንገድ ይቀይሣል፤
3. ከብሔራዊ ምክር ቤቱ ጋር የቅርብ ግንኙነቶችን በመፍጠርና ጠቃሚ ልምዶችን በመለዋወጥ የአዕምሯዊ ንብረት ዘርፍ ለልማቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ በሚያበረክትበት ሁኔታ ላይ ተቀናጅቶ ይሠራል፤
4. ከሃገሪቱ አዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ ወርክሾፖች፣ ኢግዚቢሽኖችና የመሳሰሉት የሚካሄዱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
5. በክልሉ ውስጥ የአዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ቅርንጫፍ ምስረታን አስፈላጊነት በማጥናት ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን አካል ያማክራል፤
6. በክልል አቀፍ ደረጃ የላቀ አስተዋፅኦ ያላቸውን የፈጠራ ባለሙያዎች ለማበረታታት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

2. Devise, in collaboration with the concerned bodies, a mechanism through which an infringement of intellectual property rights might be contained in the Regional State;
3. Work, in an integration with the National Council, by creating closer relations and exchanging valuable experiences, with respect to the conditions in which the intellectual property sector might contribute its own share for the development;
4. Facilitate, in collaboration with the country's intellectual property protection office, the conditions whereby workshops, exhibitions and the likes are to be undertaken in the Regional State;
5. Study the necessity of establishing in the regional state the branch of the intellectual property office and advise the body pertaining thereto;
6. Create an enabling environment to encourage those professionals engaged in creative works and have thus made outstanding contributions at the regional level;

## 6. ስለምክር ቤቱ ጽ/ቤት

የምክር ቤቱ ጽ/ቤት በክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ውስጥ የሚደራጅ ይሆናል።

## 6. Office of the Council

The office of the Council shall be organized within the Regional Capacity Building Bureau.

## 7. የጽ/ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

የም/ቤቱ ጽ/ቤት በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች

## 7. Duties and Responsibilities of the office

The office of the council shall, pursuant to this regulation have the following duties and

www.abyssinialaw.com



ይኖሩታል፦

1. ከሃገር አቀፉ የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ጽ/ቤት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር በፓተንት ሰነድ የታቀፉ የቴክኖሎጅና ሌሎች አዕምሯዊ ንብረት ነክ መረጃዎችን በሲዲ-ሮም እና በሌሎች መንገዶች አደራጅቶ ይይዛል፣ በክልሉ ውስጥ የሚከናወነውን የልማት፣ የምርምርና ቴክኖሎጂን የማላመድ ሥራዎች ይደግፋል፤

2. የፈጠራ ሠራተኞች ወደ ሃገር አቀፉ ጽ/ቤት መሄድ ሳያስፈልጋቸው የተለያዩ መመሪያዎችንና ቅጾችን ከየሚንቀሳቀሱበት አካባቢ በቀላሉ ሊያገኙ የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ የጥበቃ ማመልከቻዎችን በመቀበል ለሃገር አቀፉ ጽ/ቤት ያስተላልፋል፤

3. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በአዕምሯዊ ንብረት መስክ የሚከሰቱ የመብት ገሰሳዎች የሚገቱበትን ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም በቅንጅት ያግዛል፤

4. በብሔራዊ ደረጃ በሚዘጋጁ ወርክሾፖች እየተሣተፈ ለክልሉ የሚጠቅሙ መረጃዎች የሚገኙበትንና ባፋጣኝ የሚደርሱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

5. የአዕምሯዊ ንብረት ጉዳዮችን በተመለከተ የመወያያ አጀንዳዎችን ለም/ቤቱ ያዘጋጃል፣ የሚደረስበትም ውሣኔም በተግባር እንዲተረጐም ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

responsibilities:

1. Organize and maintain, by creating close relations with the countrywide Intellectual property protection office, technological and other intellectual property-related data embraced in the patent documents through the CD-ROM and other methods as well as support the developmental, research and technological adaptations which are undertaken in the regional state;

2. Make it favorable for those professionals with creative works to easily have an access to various directives and formats from wherever they move from with out necessarily going to the national office as well as receive and transfer to same applications for protection thereof;

3. Devise a mechanism, in collaboration with the concerned bodies, for the possible containment of an infringement of rights which may be observed in the field of the intellectual property and assist its implementation in an integrated manner;

4. Participate in workshops to be undertaken at the national level and facilitate conditions through which any information useful to the regional state might be obtained and communicated forthwith;

5. Draft the agenda for deliberation by the council on matters regarding intellectual property, cause the decision arrived at to be implemented and follow up accordingly;

www.abyssinialaw.com



6. አመታዊ የሥራ እቅዱንና የአፈፃፀም ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል።

## 8. ስለምክር ቤቱ ስብሰባ

1. ምክር ቤቱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
2. የምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ በሰብሳቢው ሊጠራ ይችላል።
3. ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ እርሱ የሚወክለው የምክር ቤቱ አባል ስብሰባውን በሊቀመንበርነት ይመራል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል 1/3ኛ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲደረግ ሲጠይቁ ከሰባት ቀናት ቀደም ብሎ ለአባላት በሚደረግ ጥሪ መሠረት አስቸኳይ ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል።
5. የምክር ቤቱ ስብሰባ በጽ/ቤቱ ይካሄዳል።

## 9. ስለምክር ቤቱ ምልዓተ-ጉባዔና የውሣኔ አሰጣጥ ስርዓት

1. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል 2/3ኛ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
2. የምክር ቤቱ ውሣኔ አሰጣጥ በጋራ በሚደረስ ስምምነት መሠረት ይሆናል።

6. Prepare its annual working plan and performance report and thereby submit same to the council.

## 8. Meeting of the Council

1. The council shall have a regular session once in three months; provided, however, that it may hold an extraordinary meeting whenever necessary.
2. The extraordinary meeting may be called for by the chairperson.
3. In the absence of the chairperson, a member of the council delegated by him shall preside over the meetings.
4. Without prejudice to the provision of sub-art 2 of this article hereof, an extraordinary meeting may be held following the request of one-third of the members of the council upon notification of the members thereof seven days in advance.
5. Meetings of the council shall be conducted in the office thereof.

## 9. Quorum and Decision Making Procedure of the Council

1. There shall be a quorum where two-third of the members of the council show up at the meeting.
2. Decisions of the council shall be arrived at through consensus.

www.abyssinialaw.com



3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር በተደነገገው መሠረት በተባበረ ድምፅ መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ በስብሰባው ላይ የተገኙት የም/ቤቱ አባላት በአብላጫ ድምፅ የደገፉት ማናቸውም ጉዳይ የምክር ቤቱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል።

4. ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሣኙ ድምፅ ይኖረዋል።

## 10. ስለ ምክር ቤቱ የተዋረድ አካላት

ምክር ቤቱ ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ውጭ ባሉና በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ታላላቅ ከተሞች እንዳስፈላጊነታቸው እየታዩ የሚደራጁ የተዋረድ አካላት ይኖሩታል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

## 11. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ምክር ቤቱ የራሱን ውስጣዊ መተዳደሪያ ስርዓት ጨምሮ ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

3. Where it has been impossible to decide on the consensus, in accordance with the provision of Sub.art.2 of this article hereof, any proposal supported by a majority vote of those members present at the meeting shall pass to be the decision of the council.

4. In case of a tie, the notion which the chairperson has voted for shall prevail.

## 10. Hierarchical Organs of the Council

The council shall, outside the regional capital city, have hierarchically subordinate organs to be established in the major urban centers, as may be necessary, Details shall be determined by a directive.

## 11. Power to issue directives

The council may issue specific directives, including its internal administrative procedure, necessary for the full implementation of this regulation.

www.abyssinialaw.com



## 12. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ነሐሴ 12 ቀን 1998 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር

## 12. Effective Date

This regulation shall enter into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State

Done at Bahir Dar

This 18th day of August 2006

Ayalew Gobezie

Head of Government of the Amhara National Regional State